# Badr MAGAZINE

# በድር መጽሔት

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው

Badr Annual Magazine Vol. III 2011



## BADR ETHIOPIA

### INTERNATIONAL ETHIOPIAN MUSLIM ORGANIZATION

# BADR AT A CROSSROADS

## The way forward

11th ANNUAL BADR CONVENTION – SAN JOSE, CALIFORNIA

# የረቃዋ ጀግና

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው

የኢስላም ታሪክ በታላላቅ ስብዕናዎች ያሸበረቀ በድንቅ ሙእሚኖች አስደናቂ ገድል የተሞላ ነው:: ከነዚህ ልብን ከሚነኩ ስለ ማንነታችን ቆም ብለን እንድናስብ ከሚጋብዙን ግን በእጅጉ ከተረሱ ታሪኮቻችን ውስጥ አንዱን እነሆ::

ታሪኩ የጀነት ባልደረቦች በዚህች ምድር ላይ ሲኖሩ ምን እንደሚመስሉ ያሳያል:: የዒባዱራህማን ገጽታን እናስተውል ዘንድ ይረዳል:: ኢማም አልጀውዚ "ሲፈቱ ሰፍዋህ" ከተሰኘው መጽሃፋቸው ውስጥ ዘክረውታል::

ነገሩ እንዲህ ነው: አቡቁዳማ ኢብን ሻሚ ታቢዕይ ናቸው:: አላህ (ሱ ወ) የጂሃድ ፍቅር ከሰጣቸው ሰዎች አንዱ ነበሩ:: ብዙ የጂሃድ መዕረካ ላይ ውለዋል:: ብዙ ተአምር አላህ በእርግጥ አሳይቷቸዋል:: ታዲያ አንድ ቀን ሃረም ውስጥ ተቀምጠው እያሉ ነበር ሰዎች ስላሳለፉት የጂሃድ ሃያት ያጫውቷቸው፣ በተለየ ትኩረታቸውን የሳበ ክስተት ይነግሯቸው ዘንድ የጠየቋቸው:: "አ! ያ አላህ! በሉ ወንድሞቼ እነግራችኋለሁ በደንብ አድምጡኝ በጣም የሚገርም ታሪክ ነው" አሉ አቡ ቁዳማ ከመቀመጫቸው እየተስተካከሉ::

"የሙስሊሞች ሰራዊት ከ 'መስቀለኞች' ጋር ለመዋጋት ወደ ጦር ሜዳ ጉዞ ላይ ነበርን:: ኢራቅ ውስጥ ከፉራት ወንዝ አቅራቢያ "ረቃህ" የምትባል ከተማ አረፍን:: በየመስጊዶቹ እየተዟዟርኩ ወደ ጂሃድ ቅስቀሳ አደረኩ:: ለሙጃሂዶች የሚሆን ስንቅም ማሰባሰቡን ቀጠልኩ:: በዚህ መልኩ ቀኑን ካሳለፍኩ በኋላ ማታ ላይ አንድ ቤት አደርኩ:: በሌሊት የቤቱ በር ተንኳኳ:: ማን ሊሆን እንደሚችል ማሰብ አልቻልኩም:: ምክንያቱም በዚህች ከተማ የማውቀው ሰው አልነበረኝምና:: ማንነቱን ስጠይቅ የሴት ድምጽ ሰማሁ:: በሩን ከፈትኩ:: "አንቺ የአላህ ባሪያ ምነው በደህናሽ ነው?" አልኳት ሙሉ ሂጃቧን የጠበቀችና ፊቷን የሸፈነች ሴት ነች::

/"አንተ አቡ ቁዳማ ነህ?"

"አዎን" አልኳት:: በከረጢት የታሰረ ነገርና ደብዳቤ ፊቴ ላይ ጥላ እያለቀሰች ሄደች:: ወረቀቱን አንስቼ ማንበብ ጀመርኩ::

"አንተ አቡ ቁዳማ ሆይ! በእርግጥ ወደ ጂሃድ ጥሪ አድርገህልናል:: እኔ ደግሞ ጂሃድ ላይ መሳተፍ የማልችል ሴት ነኝ:: ለሙጃሂድ ወንድሞቼ የምታደርስልኝ ገንዘብም የለኝም:: እናም በጣም የምወዳቸውን ሁለቱን ረጃጅም ጉንጉን ጸጉሮቼን ቆረጥኳቸው:: ለፈረስ ማሰሪያም የሚሆን ገመድ ስራሁ:: ፈረስህ ላይ ታደርጋቸው ዘንድ እጠይቅሃለሁ:: አላህ (ሱ.ወ) ጸጉሬን ፈረስህ ላይ ሲያየው ወንጀሌን እዲምርልኝና ጀነት እንዲያስገባኝ እሻለሁኝ::" (ዓጃኢብ! ኧረ እናንተ ዲኑ መች እንዲህ እንደዋዛ ደረሰና! ይህችን መሰል አስደናቂ ሴቶችን ያቀፈ ኡማ መሆኑ እንጂ ሚስጥሩ:: ኢስላምን ከራሳቸው በላይ የሚያፈቅሩ አባላት ያዘለ በመሆኑ እንጂ ዲኑ:)

አቡ ቁዳማ ትረካቸውን ቀጥለዋል::

"ከፈጅር ሰላት በኋላ ረቃን ለቀን መንቀሳቀስ ጀመርን:: ከኋላችን አንድ ወጣት በፍጥነት እየጋለበ ይከተለን ነበር::" በከፍተኛ ድምጽ ስሜን ይጣራል:: ወደ ኋላ ጠብቄ እንዳናግረው ወንድሞቼ ነገሩኝ:: ከሰራዊቱ ወደ ኋላ ቀርቼ ጠበኩት:: ፊቱን ሙሉ ለሙሉ ሸፍኗል:: "እንኳን ሳላገኝህ አልቀረሁ አልሃምዱሊላህ"

"ምን ፈልገህ ነው?" ጠየቅኩት::

"ጂሃድ መሳተፍ እፈልጋለሁ ::"

"ፊትህን ግለጠው ለጂሃድ የደረስክ ከሆንክ ከእኛ ጋር ትሄዳለህ አልያ ግን ወደ ቤት ትመለሳለህ:: ፊቱን የሸፈነበትን ሻሽ አነሳ:: ገና የ 17 ዓመት ወጣት ነው:: ልጅነቱ ፊቱ ላይ ይነበባል::

"አባትህ በህይወት አለ?" የመጀመሪያ ጥያቄዬ ነበር::

"የመስቀል ተዋጊዎች ባለፈው ዓመት ገድለውታል"

"እናትህስ አለች?"

"አዎን አለች"

"በል ተመለስና እርሷን አስደስት:: እርሷን ካስደሰትህ ጀነትን ጫማዋ ስር ታገኛለህ::"

"እናቴን አታውቃትም እንዴ አቡ ቁዳማ?"

"አላውቃትም" አልኩት::

"ባለ አደራዋን አታውቃትም?"

"የምን አደራ?" ግራ ተጋብቼ ጠየቅኩት::

"ጸጉሯን ገምዳው የሰጠችህን ሴት እንዴት በዚህ ፍጥነት ረሳሃት?"

"ያ አላህ! ታዲያ እርሷ ምንህ ናት?"

"ወሏሂ እርሷ እናቱ ነች::" እርሷው ነች ወደ አንተ የላከቺኝ:: ወደ እርሷ እንዳልመለስ በአሏህ ምላለች:: እንዲህ ነበር ያለችው:

"ልጄ ሆይ! ካፊሮች ጋር ፊት ለፊት ስትገናኝ ወደ ኋላ መመለሻ አሳጣቸው:: ነፍስህን ለአሏህ ስጥ:: የአሏህን ጉድኝት፣ የአባትህንና የአጎቶችህን በጀነት አብሮ መሆን አላማህ አድርግ:: አሏህ ሸሃዳን ሲሰጥህ ጌታዬ እንዲምረኝ ሸማግሌ ሁንልኝ:: ከዚያም ወደ ደረቷ አስጠግታ አቀፈችኝ:: አይኖቿን ወደ ሰማይ ተክላ ጌታዋን እንዲህ ተማጸነች፥ "ጌታዬ ሆይ! ይህንን ልጄን የልቤን ማረፊያ፣ የአብራኬን ክፋይ ለአንተ ሰጥቼዋለሁ:: ወደ አባቶቱና አጎቶቹ አቅርበው" ወጣቱ ከዚህ አስከትሎ "ያ አሚ!" በአሏህ ስም እጠይቅሃለሁ:: አብሬህ ከመዝመት እንዳትከለክለኝ ፥ "ኢንሻአሏህ እኔ ሸሂድ የሸሂድ ልጅ ነኝ:: የአሏህ ቃል ሙሉ በሙሉ በቃሌ ሃፍዠለሁ:: ፈረስ ግልቢያም ሆነ ጦር ውርወራ ጠንቅቄ አውቃለሁ:: እድሜው ትንሽ ነው ብለህ እንዳትንቀኝ::" ይህን ሁሉ ካለኝ በኋላ ልመልሰው አልቻልኩም:: ወደ ዘመቻው አስከተልነው::

ይገርማል'ኮ እናንተ! ምላሱ ጌታውን ከመዘከር አይቦዝንም:: ቁርኣን ከመቅራት አይለይም:: ተራራ ስንወጣ ቀድሞን የሚወጣው እሱ ነው:: ቁልቁለት ስንወርድ ተንደርድሮ ከፊት ለፊት እናገኘዋለን:: እንደ እርሱ ወኔ ያለው ከእኛ ውስጥ አልነበረም:: በዚህ መልኩ ጉዟችንን ጨርሰን ጦር ሜዳው ጋር እንደተቃረብን መሸና እረፍት አደረግን:፡ ሰራዊቱ ጾመኛ ነበር:: እናም ማፍጠሪያ ምግብ ማዘጋጀት አስፈላጊ ነበር::

"አኅቴ ሆይ! ዛሬ ምግብ የማዘጋጅላችሁ እኔ ነኝ::" አለኝ::

"አይ አንተ ይህን ሁሉ መንገድ ስትመጣ የመጀመሪያ ጊዜህ ነው፡ስለሆነ ይደክምሃል እኛ ነን የምናዘጋጀው" አልኩት::

"ወሏሂ አኅቴ እኔ ጂሃድ ውስጥ ኻዲማችሁ ነኝ እንዳዘጋጅ ፍቀድልኝ"

"እሺ ነገር ግን ጭሱ ወንድሞችህን እንዳያስቸግር ከሰራዊቱ ራቅ ብለህ ምግቡን አብስል::" አልኩት::

ሰራዊቱ ምግቡን ይጠብቃል ወጣቱ ዘገየ:: "ምን ሆኖ ዘገየ? ሂድና እስኪ እየው" አሉኝና ወደ አለበት ቦታ አመራሁ:: ምግቡ ተጥዶ እርሱግን ከሆነች ቋጥኝ ላይ ተደግፎ ሳያስበው እንቅልፍ ወስዶታል:: ታዲያ እሱ ሳይነቃ ምግቡን ማዘጋጀት ፈለግኩ:: እየሰረቅኩ ወደእርሱ እመለከታለሁ:: ወጣቱ ፈገግ አለ:: አሁንም ፈገግ አለ:: ከዚያም ፈገግታው ጨመረ:: በመጨረሻም ድምጽ ያለው ሳቅ ሳቀና ብንን ብሎ ከእንቅልፉ ነቃ::

"ውይ አኅቴ! ምግቡን አዘገየሁባችሁ? ዐፍወን::" አለና ስራውን ሊጀምር ፈለገ::

"ለምንድን ነው ተኝተህ ትስቅ የነበር? ምን ዓይነት ህልም አይተህ ነው?" አልኩት::

"አኅቴ እባክህን ለእኔና ለአሏህ ተዋት!"

"በጌታህ ስም እጠይቅሃለሁ ምንድን ነች ህልሟ?"

"አኅቴ" ብሎ ህልሙን መንገር ቀጠለ::

"አኅቴ ጀነት ገባሁ:: አሏህ(ሱ.ወ) በቁርአኑ፤ነብያችን (ሰ.ዐ.ወ) በሃዲሳቸው እንደገለጿት ከሙሉ ውበቷ ጋር አየኋት:: አንድ ከወርቅና ከእንቁ የተሰራ እጅግ በጣም የሚያምር ህንጻ አየሁና ወደ እርሱ አመራሁ:: ህንጻው በር ላይ አሳላፊዎች አሉ:: እጅግ የተዋቡ ኮረዳዎች ናቸው:: ሁሉም ወደ እኔ እየተመለከቱ ይንሾካሾካሉ:: "ይህ'ኮ ነው የመርዲያ ባለቤት!" ይባባላሉ:: ከእነርሱ ገለል ብላ የቆመችውና ከሁሉም በጣም የምታምረዋን ኮረዳ "አንቺ ነሽ እንዴ መርዲያ?" አልኳት::

"ላ! ላ! እኔ ከመርዲያ ኻዲሞች ውስጥ አንዷ ነኝ:: መርዲያን ማየት ትፈልጋለህ? አለችኝ::

"አዎን"

"ወደ ህንጻው ግባ" አለችኝ:: ገባሁ:: ያ አሏህ! ፊቷ ልክ የጸሀይ ብርሃን ያህል ያንጸባርቃል:: አሏህ ጽናቱን ባይለግሰኝ ኑሮ በውበቷ ሐይል ራሴን ስቼ በወደቅኩ ነበር:: "አንተ የአላህ ቅርብ ወዳጅ እንኳን ደህና መጣህ እኔ የአንተ ነኝ አንተም የእኔ ነህ" አለችኝ:: ደስ ብሎኝ ፈገግ አልኩ:: ከዚያም ደስ የሚያሰኙ ቃላትን ትለኝ ነበርና ፈገግታዬ ጨመረ:: እጄን ወደ እርሷ ስዘረጋ እንዲህ አለችኝ፥

"አሏህ ችግርን ሁሉ ከአንተ አርቋል የእኔ ወዳጅ:: በዱንያ ውስጥ የቀረችህ ትንሽ ጊዜ አለች:: ቀጠሯችን ነገ ከዙሁር ሶላት በኋላ ነው::" ስትለኝ ከደስታዬ ብዛት ከትከት ብዬ ስስቅ ነቃሁ::

"ማሻአሏህ ጥሩ ህልም ነው ያየኸው አልሃምዱሊላህ::" አልኩት:: በዚህ መልኩ ፈጅር ስግደን ለጦርነት ተዘጋጀን:: አሰላለፋችንን ቃኘን:: ሁሉም ሰው በወገን በወገን ተሰለፈ፥ ለመጠባበቅ ያመች ዘንድ ይህ ወጣት፥ አባት የለው ከጎኑ የሚያደርገው፣ አኅት የለው ከጎኑ የሚያስጠጋው እስኪ ልፈልገው ብዬ አሰብኩ:: በሙጃሂዶች ሰልፍ መሃል እያቋረጥኩ እፈልገው ጀመር:: አገኘሁት:: የሰልፉ መጀመሪያ ላይ ቆሞዋል:: እጁን ያስኩት፣

"አንተ ወንድሜ ከአሁን በፊት ጂሃድ ወጥተህ ታውቃለህን?"

"አይ አላውቅም"

"በል ና! መስለፍ ያለብህ መጨረሻ ነው:: ካሸነፍን ወደ ፊት ትመጣለህ:: ከተሸነፍን ለመሸሽ ያመችሃል::"

"አንተ አኅቴ ነህን? ካፊሮች ወደ ኋላ እንዲሸሹ ትቻቸው የጀሃነም ሰው እንድሆን ትሻለህ?" አለኝ::

"ጀሃነምን ሽሽት አደለም እንዴ እዚህ ድረስ የመጣነው? ልምድ የለህም ብዬ ነው እንጂ::" አልኩት:: በዚህ ሁኔታ ላይ እያለን ጦርነቱ ተጀምሮ ኖሮ ፈረስ በመካከላችን ገባና ነጣጠለን:: እርሱም ከእጄ ነጥቆ ወደ መጀመሪያው ሰልፍ ዘሎ ገባ:: ወሏሂ ወንድሞቼ ጦርነቱ ከባድ ነበር:: የአየሩ ፀባይ ሃሩር፥ ሰይፍ እጃችን ላይ አይረጋም እያቃጠለን ይወድቅ ነበር:: እጅና እግር እየተቆረጠ በአየር ሲበር ይታያል:: ብዙ ሰው አለቀ:: ይህ ወጣት ታዲያ በዚህ ሁኔታ ላይ በጽናት ይዋጋል:: ፀሃይ ዘንበል ስትል አሏህ ድል አመጣልን:: መስቀለኞች ተሸነፉ:: ዙሁር ሶላት ሰገድን:: ሁሉም ሰው የሞተበትን ፍለጋ ጀመረ:: ይህን ወጣት የሚፈልገው ሰው የለምና መፈለግ ነበረብኝ:: በጦር ሜዳው ላይ እየተዟዟርኩ በአይኔ አማትር ጀመር:: ድምጹ ይሰማኛል:: "ሰዎች ሆይ! አኅቴ አቡቁዳማን ላኩልኝ" ወደ ድምጹ ቀረብኩ:: ያ ወጣት ነው:: ፊቱ በደም ተነክሯል ያ የሚያምር ገጽታው ሌላ ሆኗል:: ሳየው ሆዴን በላኝ፡ አለቀስኩ:: የፊቱን ደም በልብሴ መጥረግ ጀመርኩ::

"አንተ አኅቴ ደሜን በልብሰህ ነው እንዴ የምትጠርገው?! በእኔ ልብስ ጥረገው::" ሲለኝ አንጀቴ ተላወሰ:: ንግግሩን ቀጠለ፣ "አልሃምዱሊሏህ፥ ኑዛዜዬን እስከምነግርህ ላቆየኝ ጌታ!"

"በአሏህ ስም እለምንሃለሁ፥ እኔ ስሞት ወደ "ሪቃ" ተመልሰህ እናቴን አሏህ ስጦታዋን (ሂዳያዋን) የተቀበላት መሆኑንና ልጇ ወደ ፊት እንጂ ወደ ኋላ ሳይል በአሏህ መንገድ ላይ እንደተታገለ እንድታበስራት:: አሏህ ከሸሂዶች ጎራ ካሰለፈኝ ሰላምታዋን ለአባቴና ለአኅቶቼ እንደማደርስ ንገራት::"

# ድንቅ አባባል

ከጀሚላ ረዲ

አሰላሙ አለይኩም ወራህመቱላሂ ወበረካቱሁ ምስጋና ለአላህ የተገባ ነው እናመሰገነዋለን እርዳታውንም እንጠይቃለን ምህረቱንም እንፈልጋለን ነፍሳችን ከምታመጣው ተንኮልና ከምግባረ ብልሹነት በእርሱ እንጠበቃለን አላህ የሚመራውን ሰው የሚያጠመው አይኖርምቅ አላህ ያጠመመውን ደግሞ የሚያቃናው የለም ከአላህ በቀር ሌላ አምላክ እንደሌለና አንድ መሆኑን እንዲሁም አጋሪ (ሽሪክ) እንደሌለው እመሰክራለሁ ሙሐመድም ባሪያውና መለክተኛው መሆናቸውን እናዘዛለው የአልህ ሰላም በርሳቸውና በቤተሰባቸው በባልደረቦቻቸውና እስከዕለተ ትንሣኤ ድረስ መልካም አርአያንታቸውን በተከተለ ሁሉ ላይ ይስፈን።

ከዐዋቂዎችም ከሞኝም ጋር አትከራከር። ዐዋቂ ያሸንፍኻል፤ ሞኝ ደግሞ ያበሳጭሃ።
የበታቹን የናቀ ግርማ ሞገሱን (ክብሩን) ያጣል።
የዕውቀት መጀመሪያ ዝም ማለት ፤ ከዚይም መስማት፤ የሰማውን መያዝ፤ ከዚያም መስራት፤ በመቀጠል ማሰራጨት ነው።

ረሱል (ሰ.ዐ.ወ.) እነዚህን ሦስት ነገሮች ባሕሪው ያደረገው ሰው ንፉግ አይባልም ብለዋል።

- ዘካትን የሚሰጥ
- እንግዳውን በሚገባ የሚያስተናግድ
- ሰዎች በተቸገሩ ጊዜ እርዳታ የሚለግሰ

ሰዕድ (ረ.ዐ.) ረሱልን( ሰ.ዐ.ወ.) ዱዓው ተቀባይ እንዲሆንለት ዱዓ ያደርጉለት ዘንድ ጠየቃቸው። ረሱል (ሰ.ዐ.ወ.) ሲመልሱ "የገቢ ምንጭህን ንጹሕ (ሐላል) አድርግ፤ ይህን ካደረክ ዱዓህ ሁሉ ተቀባይንት ያገኛል። ነፍሴ በእጁ በሆነችው ጌታ እምላለው፤ አንዲት ጉርሻ የሐራም ምግብ የተመገበ ሰው የአርባ ቀን ዲባዳው በአላህ ዘንድ ተቀባይነት አይኖረውም" አሉ።
ረሱል (ሰ.ዐ.ወ.) እንደተናገሩት "እንደ ስስት ኢሰላምን የሚጎዳ ነገር የለም" ብለዋል።
ሐቲም (ረ.ዐ.) ባግዳድ ሂደው በኢማም አህመድ ኢብን ሐንባሊ ከተማሩበኋላ ኢማሙ እንዲህ ሲሉ ጠየቋቸው:- "በዓለማዊ ፍቅር የተለከፈ ሰው እንዴት ራሱን ነፃ ማድረግ ይችላል?" ሐታም (ረ.ዐ) ሲመልሱ "ከዚህች ዓለሚዊ ፍቅርና መጥፎ ተጽእኖ ለመዳን አራት ባሕሪያት ሊኖሩን ይገባናል" አሉ። እነሱም:-

- መጥፎ ለዋለልህ ሰው መልካም በመዋል፣
  - ያለክን ከሰዎች ጋር በመከፋፈል፣
  - በሌሎች ሐብት ቀናተኛ አለመሆን፣
  - መትፎ ባሕሪ ለሚያሳይሕ ተመሳሳይ ባሕሪ አለማሳየት ናቸው።

"በጥንቃቄና በእንክብካቤ ሊጠብቁት የሚገባ ሐብት ምንድነው" የሚለውን ጥያቄ ሶሐቦች (ረ.ዐ.) ረሱልን (ሰ.ዐ.ወ.) ጠይቀው ሲመልሱላቸው:- "አላህን በማስታወስ (ዚክር በማረግ) የተጠመደ ምላስ፣ አላህን የሚፈራ ልብ፣ ባሏን በዲን ሥራ ላይ ተግታ የምትረዳ ሚስት ናቸው" ሲሉ ገልጸውል።

ረሱል (ሰ.ዐ.ወ.) ሲናገሩ "ዐዋቂ ብልህ ሰው ማለት ራሱን የሚቆታተርና ለአኼራው መልካም ሥራ የሚሠራ ነው፡፡ ደካማ ሰው ማለት ደግሞ ነፍሱ ስሜቷን ተከትላ እድሄድ ያደረገና ከአላህ ከንቱህ ምኞት የተመኘ ነው።"

ከባዱ ኃጥያት አድራጊው አቅልሎ የሚያየው ነው። የራሱን ድክመት የሚመለከት ሰው የሌሎችን ስህተትና ድክመት አይመለከትም። አላህ በሰጠው ሲሳይ የሚረካ ሰው በሌለው ነገር አያዝንም።

ዓሊ (ረ.ዐ.) "አራት ነፈሮች እስካሉ ድረስ ሃይማኖትና ዓለማዊ ሕይወት ተነጣጥለው አይወድቁም" አሉ። እነሱም:-

- በዕውቀቱ የሚሰራ ዓሊም፣
- መማርን የማያፍር መሃይም፣
- ለመመጸወት ሰስትና ንፍገት የማየገታው ሐብታም፤
- የአኺራውን ያማረ ሕይወት ለዱንያ ጥቅም ሲል አሳልፎ ያልለወጠ ድሃ እሰካለ ድረስ።

ነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ.) ሲናገሩ:- ጂብሪል (ዐ ሰ)

- ስለ ጉርብትና ሐቅ ውርስ ይገባቸዋል ይል ይሆናል ብዬ እስከጠራጠር ድረስ አደራ ብሎኛል።
- ስለ ሴቶች አጥብቆ ሲነግረኝ (አደራ ሲለኝ) ፍቺ ይከለከል ይሆን እስክል ሰጋሁ።
- ስለ መፋቂያ አስፈላጊነት ሊገልጽልኝ ግዴታ ሊያደርግ ይሆን ስል ሰጋው።
- ስለ ሶላተል ጀመዓ አጥብቆ ሲነግረኝ ሶላት ያለ ጀመዓ ተቀባይነት አይኖረውም ይለኝ ይሆን ስል ሰጋሁኝ።
- ስለ ዚክር አስፈላጊነት ሊገልጽልኝ ያለ እርሱ መልካም ሥራን ውድቅ ሊያደርገው ይሆን እስክል ነበር የሰጋሁት አሉ።

ነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ.) ሲናገሩ "ይህችን ዓለም በልቡ ባፈቀራት ሰው ላይ አላህ (ሱ ዐ) አራት ነገሮችን በልቡ ላይ ያኖርበታል" አሉ።
እነሱም:-

- የማይለቀው ስጋት፣
- ነፃ ያልሆነ ሕሊና (እረፍት የሌለው ሥራ)፣
- የማያልቀውን ድህነትና
- የማይረካበት ተስፋ ናቸው።

ጓደኛህ ከአንተ ከዕድሜ የበለጠ ከሆነ በአክብሮት ተወዳጀው።

- ከአንተ አቻ ከሆነ በስጦታ ተወዳጀው።
- ከአንተ በኑሮ ዝቅ ካለ በመተዛዘን ተወዳጀው።
- ከአንተ በዕውቀት ከበለጠከ አገልጋዩ በመሆን ተወዳጀው።
- ከአንተ ያነሰ ዕውቀት ያለው ከሆነ በዘዴ ተወዳጀው።
- ከአንተ በሀብት የላቀ ከሆነ ለዱንያ ደንታ የሌለው ሰው ሆነህ ቅረበው።
- ከአንተ ያነሰ ድሃ ከሆነ ለጋስ ሆነህ ተወዳጀው።

ሱፍያን አስ ሠውሪ (አላህ ይዘንላቸው) እንዳሉት "ሸይጣን በሰው ልጅ ላይ የበላይነት የሚከዳጀው ድህንትን ማስፈራሪያ በማድረግ ነው። በዚህ ድል የሆነለት ሰው ለኃጥያት እጁን የሰጠና የእውነትን ትጥቅ የፈታ ነው። በምኞቱ አዳሪና በፈታሪውላይ እምነት በማጣት ልቡ በጥርጣሬ የተሞላ ነው።"

ዐብደላህ ኢብን ዑመር (ረ. ዐ) "ዱንያን ከኪስ እንጂ ከልብህ አታኑራት" በለዋል።

ዓሊ ኢብን አቡጧሊብ (ረ .ዐ) ሲናገሩ አምስት ነገሮች የዚህች ዓለም መገለጫዋች ናቸው።

- የወዳጅ በሞት መለየት፣
- የሐፍትና ንብረት መውዳም፣
- በጠላት ስር መውደቅ፣
- የረጅም ጊዜ ሕመም፣
- ተንኮለኛ (ነገረኛ) ሚስት።

<u>አምስቱ የወድያኛው ዓለም (ያ አኺራ) መከራ መገለጫዎች ናቸው።</u>

- ያለ ምክንያት በኢማም አሰጋጅ ነት ያለመሰገድ (ጀመዓ ማሳለፍ)፣
- የዓሊም ሞት፣
- አላህን ጠይቆ አለማግኘት፣
- ወላጅን በክፋት መለየት፣
- ዘካን መከልከል።

<u>አምስት ነገሮች ዕድሜ ቀጣይ ናቸው።</u>

- ዝምድናን መቀተል፣
- ለወላጅ በጎ ነገር መስራት፣
- በሌሊት ሶላት መስገድ፣
- ዱዓን ማብዛት።

በጊዜ ወደ መኝታ መሄድና በማለዳ ከእንቅልፍ መንቃት የሰው ልጅን ጤናማ፣ ባለፀጋና ብልህ ያደርጋል።

ዑስማን (ረ .ዐ) ሲናገሩ፡- "አላህን ከልብ የሚያውቁ ሰዎች የሚከተሉትን ባሕሪያት ይወርሳሉ። እነሱም፡-

- ልባቸው አላህን በመፍራትና ከአላህ በመከጀል ይስፀናሉ።
- ምላሳቸው አላህን በማመስገን በማወደስ ያዘወትራሉ።
- ዓይናቸው ሐያእ በማድረግና አልቅሶ በመለመን (ከአላህ) ያገኛሉ።
- ምርጫቸው ሁሌም ለዱንያ መጨነቅና እርሷን ማርቀር ሳይሆን የ አላህን ፀጋ መፈለግ ይሆናል።

ወሃብ ኢብን አብ ሙናባህ (ረ .ዐ) ሲናገሩ፡- "ኢማንህ እርቃኗን እንዳትቀር የአላህ ፍራቻ አልብሳት፤ በሐያእ አጊጣት፤ በ አላህ ፍጥረታት ላይ በማስተንተንና በማድነቅ (ተፈኩር በማድረግ) ካፒታሏን ተቀማጭ አድርግላት" ሲሉ መከረውል።

ዓሊ ኢብን አቡ ጧሊብ (ረ. ዐ) ሲናገሩ፡- "እውነተኛ ጓደኛ በሦስት ነገር ይፈተናል" አሉ።

- በችግርህ ጊዜ፤
- አንተ በሌለህብት ጊዜ፤
- ከሞትከ በኋላ በሚያደርጋቸው አድራጎቶች።

በጀነት ውስጥ አራት ነገሮች መገኘት የጀነትን ደረጃ ያልቁታል፡-

- ጀነት ውስጥ መግባት ሲያሰደስት ከዚያ ያለመውትጃቱ ደግሞ ከመግባቱ በልጦ ደስታ ይሰጣል።
- ጀነት ውስጥ ከመግባት የሚያስደስተው መልአክ አገልጋይ ሆኖ መመደቡ ነው።
- ጀነት መግባት ሲያስደስት ከዚያ ይበልጥ የሚያስደስተው የአላህ ዉዴታ ማግኘት ነው።
- በጀነት መግባት አስደሳች ሆኖ እያለ ከዚያ ይበልጥ የሚያስደስተው ከነብያቶች ጋር መሆን ነው።

በጀሃነም ውስጥ አራት ነገሮች መገኘት የጀሃነምን የከፋ ደረጃ ያሳያሉ።

- ጀሃነም ውስጥ መግባት አስከፊ ሲሆን፤ ከዚያ አለመውጣቱ ደግሞ በጣም የከፋ ነው። (አላህ ይጠብቀን)
- ጀሃነም ውስጥ ከመግባት በጣም የሚያስከፋው በመልአከ ያለመካደሙ ነው።
- ከጀሃነም የሰይጣን ጓደኝነት ማበጀቱ ነው።
- ከጀሃነም መግባቱ የከፋው የ አላህን ቁጣ ማየት ነው።

አላህ ከጀሃነም ይጠብቀን አሚን።

ዐሊይ ኢብኑ አቡ ጧሊብ (ረ.ዐ) ሲናግሩ፡-

- አላህ ያልፈሩበት ሶላት፤
- ከንቱ ንግግር ያላስውገዱበት ጾም፤
- አዘውትረው ያለነበቡት ቁርአን፤
- ያልሰሩበት እውቀት፤
- ያለገሱበት ሐብት፤
- ያልተፋቀሩበት ጓደኝነት፤
- ያልተብቃቁበት ጸጋ፤
- ኢኽላስ የሌለለብት ዱዓ ጥቅመቢስ ናቸው፡ ብለዋል።

የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ሲናገሩ፡- "ሕዝቦች አምስት ነገሮችን በመውደድ ከአምስት ነገሮችይዘነጋሉ" ካሉ በኃላ ሲዘራዝሯቸው።

- ሕይወትን ያፈቅሩና ሞትን ይረሳሉ፤
- ዱንያን ያፈቅሩና አኼራን ይዘነጋሉ፤
- ህንፃ መገንባት ይወዱና ቀብር መኖሩን ይዘነጋሉ፤
- ገንዙብ ይወዱና ከሒሳብ (በቂያማጊዜ መተሳሰቡን) ይዘነጋሉ፤
- ፍጡራንን ያፈቅሩና ፈጣሪን ይዘነጋሉ።

አላህ ከዚህ ይጠብቀን! አሚን::

የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ሲናገሩ፡- “ሦስት ዓይነት ሰዎች አላህን ይለምናሉ፤ ግን ተሰሚነት አያገኙም” አሉ እነሱም፡-

- ምግባረ ብልሹ ሚስት ኖሮት የማይፈታት፤
- ለቲሞች (ልሙት ልጆች) ለ አካል መጠን ሳይደርሱ ንብረታቸውን ራሳቸውን እንዲያስተዳድሩ መልሶ የሚሰጥ፤
- ያለ ምስክር ለሰው ገንዘብ የሚያበድር ሰው ናቸው።

ዐሊይ ኢብኑ አቡ ጧሊብ (ረ.ዐ) ሲናገሩ፡- “አንድ የአላህ ባሪያ በሥራው ከሚያገኘው ይልቅ በኒያው (በልቡ ካሰበው) የበለጠ ዋጋ ያገኛል። ምክንያትይም ኒያ ታይታ (ሪያእ) የለውምና” ብለዋል።

ዐሊይ ኢብኑ አቡ ጧሊብ (ረ.ዐ) ሲናገሩ፡- “ስድስት ነገሮችን ያደረገ ሰው ለጀንት ይበቃል፤ ከዐዛብም ይጠበቃል” አሉ። እነሱም፡-

- አላህን አውቆ ለትዕዛዙ ያደረ፡
- ሰይጣን አውቆ ከተንኮሉ የተጠነቀቀ፤
- አኼራን አውቆ ሰንቅ ያዘጋጀ፤
- ዱንያን አውቆ በዱንያ የሰራበት፤
- እውነትን አውቆ የተከተላት እና
- ሐሰትን አውቆ የራቃት ናቸው

ዑስማን ኢብን ሀፋን (ረ.ዐ)፡- “ጥፍጥና ባራት ነገሮች አግኝው” አሉ።

- አላህ ያዘዘውን ግዴታ በመፈጸም፤
- አላህ ከከለከለውና ሐራም ካደረጋቸው ነገሮች በመራቅ፤
- አላህ በመልካም ያዘዘውን ነገር መሥራት፤
- አላህ የሚጠላውን ነገር መሥራት የ አላህ ቁጣ ስለሚያመጣ ፈርቶ በመተው ናቸው።

ኢብኑ ዑመር የአላህ መልዕክተኛ (ሰ. ዐ .ወ) ትከሻዬን ያዝ በማደራግ፡- “በዚህ (አለም ስትኖር) እንደ እንግዳ ወይም እንደ መንገደኛ ሁን” አሉኝ በማለቱ ተዘግቧል።

አራት ነገሮች አሉ። ላዩን ስናያቸው ምንዳ ያላቸው ውስጡን ስንመለከታቸው ግን ግዴታ መሥራት ያለብን ነገሮች ናቸው። እነሱም፡-

- ከአላህ ሰዎች ጋር አብሮ መኖር፤
- ቅዱስ ቁር አን መቅራት፤
- ቀብርን መጎብኘት እና
- የታመመን ሰው መጠየቅ ናቸው።

ዐሊይ ኢብኑ አቡ ጧሊብ (ረ.ዐ) እንዲህ ሲሉ ተናግረዋል፡-

“ጀነትን የፈለገ ሰው በኸይር ሥራ መሽቀዳደም አለበት።”

ከዐዛብ ለመዳን የፈለገ ሰው ልቦናው የሚከጅለውን ሁሉ ከመፈፀም መቆጠብ አለበት። ስሜቱን መቆጣጠር ያሻል።

ሞት አይቀሬ መሆኑን ያመነ ሰው የዱንያ ጥቅም (ፍቅር ነዋይ) ልቡ አይገባ።

ዱንያ ጠፊ መሆኗን ያውቀ ሰው በመቸገሩ የሚያጋጥመው መከራ ምንም አይመስለውም።

ዑቅባህ ኢብን አሚር (ረ.ዐ.) ረሱልን (ሰ.ዐ.ወ.) የምድ'ንበትን መንገድ ጠየቅኳቸውና እንዲህ ሲሉ መከሩኝ፡- “ምላስህን ተቆጣጠር፤ ቤጥ ይቻልህ፡ ለኃያጠኛ አልቅስ” አሉኝ።

ሀብደላህ ኢብን መስዑድ እንደተናገሩት “አራት ነገሮች የቀልብ ጨለማን ያመጣሉ (ያስከትላሉ)።” እነሱም ፡-

- ያለቅጥ ጠግቦ መብላት፤
- ከአጥፊና ኃጢያተኛ ጓደኛ ጋር መግጠም፤
- ያለፈ ወንጀልን ያለማስታውስ እና
- በማይቋጭ ምኞት መባዘን ናቸው።

አላህ የወደደው ሰው ምልክቱ አራት ነው። እነሱም፡-

- ያለፈውን ኃጢያት እያስታወሰ ተውበት ማድረግ፤
- ያለፈውን መልካም ሥራ ሲያስታውስ ያነሰ መሆኑን አውቆ ተጨማሪ መልካም ሥራ መሰራት፤
- በዱንያ የበላዩ የሆነውን ሰው ከማየት ይልቅ በኢማን የበለጠውን ሰው እያየ እንደርሱ ለመሆን መጣር፤
- በዱንያ የበታች የሆኑትን እያዩ አላህን ማመስገን ናቸው።

ሐቲም እንዲ ብለውል፡- አራት ነገሮችን ፈልገው ሌላ አራት ነገሮችን ካላሟሉ ምኞት ከንቱ ሆኖ ይቀራል።

- አላህን እወዳለው ብሎ አላህ ከከለከለው የማይርቅ ሰው ምኞቱ ከንቱ ነው።
- ምስኪንን እየጠሉ ነብዩን እወዳለሁ ቢሉ ከንቱ ምኞት ነው።
- ጀነትን እወዳለሁ ብለው ሶደቃን የማይሰጡ ከሆኑ ምኞቱ ከንቱ ነው።
- እሳትን እፈራልሁ ብሎ ኃጥአትን በመስራት ትላይ የሚገኝ ሰው ምኞኡ ከንቱ ነው።

ረሱል (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲ ብለዋል፡- የኔ ኡመት (ተከታዮች)

- ለዓለማዊ ፍቅር በቀረቡ ቁጥር የኢስላም ክብርና ሞገስ ከልባቸው ይጠላሉ።
- በመልካም ማዘዝን ከመጥፎ መከልከልን ባቆሙ ገዜ የአላህ ቅዱስ መንፈስ ይሸሻቸዋል።
- ለኃጢያት የጋራ መሰማማት ባደረጉ ጊዜ ከአላህ ዓይን ተዋርደዋል።>>

ከማርጀትክ በፊት የወጣትንት ጊዜህን፥ ጤናማነትን ከመታመምህ በፊት ቁም ነገር ላይ አውል።

የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲ ሲሉ መናገራቸውን ሐዝራት አቢ ሰዒድ አል ኹድሪይ ገልፀዋል። “የአዳም ልጅ ከእንቅልፉ ሲነቃ አካላቱ ሁሉ ምላሱን እንዲህ ሲሉ ይማፀናሉ።”

- እኛን በተመለከተ አላህን ፍራ፤ ምክንያቱም እኛ የምንከተለው አንተን ነውና።
- አንተ ከተስተካከልክ እኛም እንስተካከላለን፡ አንተ ከተሳሳትክ እኛም እንሳሳታለን።

ነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ.) “የሰው ልጅ ሲያረጅ በውስጡ ሁለት ነገሮች ወጣት ሆነው ይገኛሉ፤”

- ስስታመነትና
- ረጅም ዕድሜ መመኘት ናቸው።”

ረሱል (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲ ሲሉ መናገራቸውን ዐሊ (ረ.ዐ.) አስተላልፈዋል። “ዝምድናውን የቀጠል ሰው ለአራት ነገር ዋስትና እገባለታለው፡-”

- ረዥም ሕይወት እንደሚኖር፤

• ከዘመዶቹ መካከልም እንደሚከበር፤
• ሪዝቁ እንደሚሰፋ እና ጀነት እንደሚገባ።>>

አንድ ሰው ወደ ረሱል (ሰ.ዐ.ወ.) ዘንድ መጣና፦ "እባክዎን የማልረሳውና ተግባራዊ ሳደርገው የምችለውን አጥር ምጥን ያለ ምክር ይለግሱኝ" ሲል ይጠይቃል። ረሱልም (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ ሲሉ መከሩ፦

• ሶላትህን በምትሰግድበት ጊዜ የመጨረሻህ ሶላት እንደሆነ አድርገህ ቁተር።
• የኃላ ኃላ እንድታዝን የሚያደርግህን ነገር ከመናገር ተቆጠብ።
• ሌሎች ሰዎች ባገኙት ሀብት የናት መንፈስ አታሳድር።

ዑስማን ኢብኑ ዐፊብ (ረ.ዐ.) ሲናገሩ "በወርቅ በተፃፈ የከበረ ቅርስ ላይ ሰባት ነገሮች ተጽፈዋል" አሉ።

• የሰው ልጅ ሟች መሆኑን እያውቀ ሳቅ ማብዛቱ፤
• ይህች አለም ጠፊ መሆኗን የመኖር ፍላጎቱን ማስረዘም፤
• ሁሉ ነገር በቅድሚያ ተወስኖ መገኘቱን እያወቀ አንዳች ነገር በጠፋ ቁትር ሀዘኑ መበርታቱ፤
• የገሀነም እሳት አስከፊ መሆኗን እያወቀ በኃጢያአት ላይ መገኘቱ፤
• በነገው በአኼራው ሕይወቱ፤ በሃብቱ የሚተሳሰበው ፈጣሪ እያለ በዚህች ዓለም ሃብቱን በማግበሰበስ መቆለሉ፤
• በአላህ አምናለሁ እያለ ከእርሱ ሌላ ያለውን የሚከጅልና የሚያስታውስ መሆኑን፤
• በጀነት ፍሰት መኖሩን እያመነ በዚህች ዓለም መደሰቱን መምረጡን ያስገርማል።

"ትዕግስት ገበናን ሸፋኝ ነው። ጥበብ የሰላ ሰይፍ ነው። ስለዚህ ድከመት ህን በትዕግስ ሸፍነው። ከንቱ ምኞትን በጥበብ (ሰይፍ) ግደለው።" ዐሊይ ኢብኑ ጧሊብ

አቡ ዘር (ረ.ዐ.) የ አላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ ሲሉ መከሩኝ አሉ፦ "ዝምታ ማብዛት አለብህ፤ ምክንያቱም ዝምታ አላስፈላጊ ከሆኑ ነገሮች በመታቀብ ሰይታንን የሚያባርርና ሃይማኖትን (የኢስላምን) ከንዋኔዎች ለመፈጸም የሚረዳህ ነው።"

የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) የኢማን ጥፍጥና የሚገኘው በሦስት ባሕሪያት እንደሆኑ ተናግረውል። እነሱም፦
• አላህንና መንዕክተኛውን ከምንም በላይ መውደድ፤
• አንድ ሰው ሲወዱ ለአላህ ብቻ ብዕለው መውደድ፤
• ወደ ክህደት መመለስን ልክ እሳት ውስጥ የመግባት ያህል መጥላት ናቸው።

መናገራቸውን ሀዘረት ኢብኑ ዑመር (ረ.ዐ.) አስተላልፋል። "እናንተ ሴቶች ሆይ ! ምፅውት አብዙ፡ የ አላህን ምህረትም በብዛት ጠይቁ፡። ገሀነም ከገቡት ውስጥ ብዙዎቹ ሴቶች ናቸውና" ሲሉ፣ ከሴቶቹ ውስጥ አንዷ "ከገሀነም ሰዎች አብዛኛዎቹ ሴቶች የሆኑት ምን ወንጀል ቢሠሩ ነው" ስትል ጥያቄ አቀረበች። ረሱል (ሰ. ዐ .ወ) ሲመልሱ፦
እርግማን ስለምታብዛና ባሏን ስለማትታዘዝ ነው አሉ።

{ አላህ ይጠብቀን አሚን! }

"ሦስት ሰዎች ጀነት አይገቡም" አሉ የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.)። እነሱም፦
• እታላይ፤
• ሰሰታም እና
• በእጁ ያለውን ንብረት ያለአግባብ የሚጠቀም። (ቲርሙዝ)

ረሱል (ሰ.ዐ.ወ.)፦ "የመናፍቃን ምልክቶች ሦስት ናቸው" አሉ።
• ሲናገር ይዋሻል፤
• ቃል ኪዳን ሲገባም ቃሉን ያፈርሳል (አያከብርም)፤
• ሲታመን ይከዳል።

የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ከስራዎች የላቀ ሥራ ምንድ ነው? ተብለው ሲጠየቁ፤
ከሐራም መከልከል ነው። ምላሰን ተቆጣጠራት፤ አላህን ዘውትር በማውሳት አርጥባት አሉ።

ከጓደኛ ምርጡ ማነው? ተብለው ሲጠየቁ
"አላህን እንድትፈራ ይሚያስታውስህ፣መልካም ሲሰራ ስታየው ተግባሩን የምትከተል፤
ለችግርህ ስትጠራው የሚደርስልህ ነው" አሉ።

ከሰውሰ ተንኮለኛ (መጥፎ) ማን ነው ተብለው ሲጠየቁ "የዐዋቂ አጥፊ ነው" አሉ።
ኢብን ዑመር (ረ.ዐ.) እንዳወሩት የአላህ መልዕክተኛ (ሰ ዐ ወ) ትከሻዬን ያዝ በማድረግ፦ "ዐብደላህ ሆይ" አሉኝ። "በዚህች ዓለም ስትኖር እንደ እንግዳ ወይም እንደ መንገደኛ ሁን።" በተጨማሪም "ካመሸህ ንጋትን አትጠብቅ፤ ከጤንነት ለሕመምህ፡ ከሕይወት ደግሞ ለሞት ማሰቢያ ጊዜ ውሰድ" አሉኝ።

"አቡዘር ሆይ" አሉ ረሱል (ሰ.ዐ.ወ.)። "በራስ መብቃቃትን የመሰለ እውቀት የለም፤
ከሐራም መራቅን የመሰለ አላህን ፈሪነት የለም፤በመልካም ባሕሪ መገኘትን የመስል የለም።"

የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ ሲሉ ተናግረዋል፦ "አላህን ጠብቀው፡ ከፊትህ ታገኘዋልህ፤
ከ አላህ ጋር በሰላም ጊዜ ተዋወቅ፡ በችግርህ ጊዜ ያውቅ ሃል፤ያላጋጠመህ ነገር ሊደርስብህ እንዳልነበረ፡ የደረሰብህ ደግሞ ሊያልፍህ እንዳልነበር እወቅ ድል ከትዕግስት፤ እርካታ ከጭንቀትና ችግርም ከምቾት ጋር መኖሩን እወቅ።" ቲርሙዝ

የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ስለገነት (ጀነት) ሲገልፁ እንዲህ ብለዋል፦
"• የዘላለም ጤንነት የሚገኝበት በሕመም መሰቃየት የሌለበት፤
• የዘላለም ህይውት የሚገኝበትና ሞት የማይደርስበት፤
• ዘላለም ውታት እንደሆኑ የሚኖሩበትና እርጅእና የማይመታበት፤
• የተሟላ ደስታ መንናደፍያና ነፍስ ሌላ የማትከጅልበት ነው።"
አላህ ይውደዳቹ

# Where is Justice for the Muslims of Axum?

By: Ethiopian Muslims from Tigray – Diaspora

As Ethiopian Muslims from Tigray living in the Diaspora, we must strive to bring to light both the extent and the causes of the blatant discrimination and injustice that is inflicted upon the Muslim population in Axum.

Both Muslims and Christians fought alongside one another for a common cause under the Tigray People's Liberation Front (TPLF) and later the Ethiopian People's Revolutionary Democratic Front (EPRDF) to bring an end to the dictatorial Derg military regime. Although this common struggle for freedom cost the lives of thousands of Muslims and Christians, it culminated into a victory shared by all Ethiopians. The 1991 victory was greeted with joy throughout the country, especially within the Muslim community.

The Muslims of Axum endured many difficulties as they strived to establish a formal house of worship within the vicinity of Axum. The twenty-thousand Muslims of Axum sacrificed their blood, sweat, and tears in the struggle for freedom against the Derg military regime, and even today Ethiopian Muslims are among the ranks of the state military from low-ranking officers all the way to Generals in the Ethiopian National Defense Forces. In spite of these accomplishments, Muslims in Axum still do not even have the right to practice their religion in their own hometown.

After the demise of the Derg military regime, officials of the current local government moved to institutionalize religious inequality in Axum by denying Muslims some of the most basic rights: rights to build Mosques, schools, and even preventing Muslims from attending funeral processions outside of Axum.

Although in the Ethiopian Constitution of 1995, Article 27 specifically grants equal religious rights to all Ethiopian citizens. Ethiopian Muslims of Axum have fallen victim to a discriminatory system which has turned them into second-class citizens within their own town.

The US State Department in 2007 wrote, *"Local authorities in the northern town of Axum, a holy city for EOC. continued to deny Muslim leaders' repeated requests to allocate land for the construction of a mosque, even though the Constitution provides for freedom to establish institutions of religious education and administration. Tigray and Amhara regional government officials chose not to interpret this provision liberally in the towns of Axum and Lalibela respectively and the Federal Government did not overrule them. Muslims have had access to land since the country became a republic in 1995."*

In addition, a blatant campaign to eliminate the city of its Muslim and Pentecostal populations is already underway. Let us briefly depict the nature of the discrimination directed towards the Muslim community in Axum by outlining four incidents and their aftermaths.

**The first incident:** It began on August 14, 1991, a group led by a former guerrilla fighter, Haile Reda, vandalized Muslim homes in Axum, desecrated Qur'ans, and even assaulted women, children, and the elderly under unfounded allegations that the entire Muslim community in Axum planned to build a Medressa (Islamic School) in the city. Current president of the Tigray region, Mr. Tsegay Berhe, and the chief for the Bureau of Urban and Agricultural Development, Mr. Abay Woldu, were both sent to Tigray as envoys from Addis Ababa to mitigate the situation rather than to address it. Both men assured the Muslim community in Addis Ababa in writing that the problem would be resolved as soon as a permanent government was established. However, once they assumed their respective posts in the newly formed government, they abandoned their promise to resolve the problem. In fact, it was later discovered that Mr. Abay Woldu was the vanguard of the campaign against the rights of Muslims. In a fare-well speech he gave when he was promoted from his Central zone administrative post to a higher position in the Tigray regional government, Mr. Abay Woldu made it clear that he see to it that the campaign against Muslims in Axum would continue. He promised his supporters that he would oversee it from his new office in Mekele.

**The second incident:** During the beginning of the month of Ramadan in 2003 (early November), six members of the Muslim community of Dura, a town located 7 kilometers away from Axum, were detained and charged with conspiracy to renovate a seventy-five year-old Mosque. There was no evidence of any plans to renovate that Mosque. Although they were released after an arduous process, the mosques fate was horrifying; it was demolished by armed men. What was even more abhorring were the comments made by the town's administrator who stated, *"We released you so you could witness this destruction with your own eyes, not because we cared about your well-being."* In addition, arms were confiscated by the local government from every Muslim militiaman a day before the action took place leading to assumptions that the government and military were behind the demolition of the mosque. Axumite Muslims living in Addis Ababa at the time were outraged by this horrible crime and appealed to Prime Minister Meles Zanawi. The Prime Minister promised that he would assign a commission to investigate the situation and expunge the roots of the problem. He vowed that the

perpetrators of this heinous crime and their accomplices would be brought to justice.

Today, seven years since the demolition, not one of the perpetrators have been brought to justice, the Mosque remains in ruins.

**The third incident:** In a gesture of outrage over what happened in Dura, Axum, Axumite Muslims living in Addis Ababa mobilized and formed an association called the Mutual Development Association of Muslim Natives of Axum and its Vicinity. It was not until 2003 that the Association finally received official recognition from the Ministry of Justice, after an uphill battle. Since permits to conduct Islamic-related projects were prohibited in Axum, the Association drafted a plan to initiate secular programs and began to raise funds to build a school. In order to implement the initiative, the Association was granted 4200 square meters of land by the mayor of the city. However the city engineer forced the association to discontinue the project even though the land-leasing fee had already been paid and the process of purchasing building materials was already underway. The mayor that had initially given the permit was removed from his post. Members of the association went to numerous offices to appeal the decision. When a representative of the association asked the new mayor, Mr. Negash, for an explanation he gave a disturbing reply. He explained, "*Muslims and Pentecostals will not occupy places in Axum; do not waste your energy.*" It is unfortunate to hear such a degrading and dehumanizing comment from a person of authority, one who is trusted with major civic responsibilities. When asked in public, the Mayor admitted that he made the comment so that he would not be badgered by the question any longer. In the mean time, in a gesture of disrespect towards the association, the mayor announced that he would confiscate the school along with its materials.

**The fourth incident:** Despite the repeatedly denied permission to build a mosque, permission was granted to congregate in a private residence. However, on the eve of the 2006 Eid-ul-Fitr celebration, unknown individuals trespassed into the private house and assaulted the worshipers. As a result of this assault, a member of the Ethiopian Muslim community, Mr. Abdul-Aziz Wehab was in critical condition. As if that was not enough, the aforementioned household was vandalized three days later at 2:15 a.m. by unidentified men. Mr. Abadi Zemo, vice president of the Tigray region and a native of Axum was sent to investigate and to mediate the situation. But shockingly, Mr. Abadi gave a threatening speech to a crowd of both Muslims and Christians declaring that there would be consequence for anyone who plans to build a mosque in the Axum Area. His speech angered the Muslim community and intensified an already rampant tension. Due to all these incidents, Axum has since become the only place in the world with Muslim population that is unable to practice their religion freely.

Muslims of Axum and its vicinity elected officials of all levels of the government under the impression that they would represent their best interests. Muslims of Axum participated in the effort to overthrow the Derg regime in the hopes that they would finally attain full freedom from tyranny and oppression, however to this day that freedom has been continually denied to them. In fact, the right they gained to purchase land and to build residences under the former regime, has been threatened since the local government came to power.

We can no longer handle these threats by ourselves. Therefore, putting the severity of the situation and its consequences, which undoubtedly can result in a full-blown conflict, into serious consideration, we the Muslim natives of Axum, heretofore draft and present appeal to the Federal Government of Ethiopia.

*We, the Muslim Community of Axum and its vicinity ask the Federal Government to intervene by having a serious discourse with us, in a forum that will develop a holistic approach to addressing the issues and their underlying causes. The purpose of this meeting will be to ensure that the constitutionally-guaranteed religious rights of all Muslims in Ethiopia are respected and assured so that we can live alongside our neighbors with respect, tolerance, peace and harmony.*

In conclusion, we would like to draw attention to the fact that, despite the efforts of certain unscrupulous government officials, the people of Axum have both lived in harmony and have shown respect for one another for centuries. Most residents are aware of our shared history and the ties that bind us together, which transcend our different faiths.

Indeed, we should have exposed this injustice to the Ethiopian people and even to the world community sooner. Now, we are convinced that our prior inaction has led us to this current predicament, we hope that we can find a solution to this injustice through our own initiative. This is a sincere plea for you to help us in any way you can to end our struggle against this injustice.

We urge, in the name of Allah, the citizens of Ethiopia and of the world to understand our predicament, to sympathize with our plight, and to mobilize by assisting us with any means possible.

Ethiopian Muslims from Tigray – Diaspora

We can be reached for any questions at

muslimaksum@yahoo.com.

# BADR ETHIOPIA

**AN INTERNATIONAL ETHIOPIAN MUSLIM ORGANIZATION**

4701 Sangamore Road, Bethesda, MD 20806

Tel. 202-465-4779 - E-mail: badr@badrethiopia.org - www.badrethiopia.org



**Masjids are burning to the ground in Ethiopia.**



**Who instigated the church burning?**



**Who is behind all of this?**

**Please send your donation to the "Burnt Masajid Fund Reconstruction Program" Badr Ethiopia. For more information visit www.badrethiopia.org**

የበድር አባል በመሆን አገራችንና ሕዝባችንን እንደግፍ የአንድ ዓመት ክፍያ
60 ዶላር ብቻ ነው ድህረ ገፃችንን ወይም ቢሮአችንን ይጎብኙ

PLEASE HELP BADR'S PROJECTS AND ITS GROWTH

*BY BECOMING A MEMBER*

Annual membership fee is only $60. To be a member visit **www.badrethiopia.org**